- ቀደም ሲል ሰዎች የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ኢየሱስን ሲጠይቁት ምን አላቸው?

ዮሐንስ 6፡28-29

28- እነርሱም «ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመስራት ምን ማድረግ አለብን?» አሉት።

29- ኢየሱስም፥ «እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ፥ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው» ሲል መለሰላቸው።

- የዘላለም ሕይወት ለማግኘት መስራት ያለብን ብቸኛ ሥራ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው።

- ከክፉ ልባችን ሊያድነን የሚችለው ማን ብቻ ነው?

- ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።



ትምህርት 62

1. ኢየሱስ የአልዓዛርን መታመም እንደሰማ ወዲያውኑ ያልሄደው ለምን ነበር?

ሀ- ኢየሱስ አዳኝ አምላክ በመሆኑ ታላቅ ኃይሉን ሊያሳይ ስለፈለገ ነበር።

2. ማርታ ያሰበችው ኢየሱስ በመጨረሻው ቀን አልዓዛርን ከሞት እንደሚያስነሣው ነው። ኢየሱስ ያለው ይህንን ነበር?

ሀ- አልነበረም።

3. ማርታ የመጨረሻ ቀን ስትል ምን ማለቷ ነበር?

ሀ- የመጨረሻ ቀን በዘመን ፍጻሜ የሞቱት ሰዎች ሁሉ ከሞት ወደ ሕይወት የሚሸጋገሩበት ጊዜ ነው።

ለ- በመጨረሻ ቀን እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ስለሰሩት ኃጢአት ይፈርድባቸዋል።

4. አልዓዛር ከሞት ለመነሣት የመጨረሻውን ቀን መጠበቅ የሌለበት ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም ትንሣኤና ሕይወት የሆነው ኢየሱስ በዚያ ስለነበር ነው።

5. ኢየሱስ በእርሱ የሚያምን ሁሉ ቢሞት እንኳን ህያው ይሆናል አለ ሰው ከሞተ በኋላ በሕይወት የሚኖረው እንዴት ነው?

ሀ- ኢየሱስ በእርሱ የሚያምኑ በስጋ ቢሞቱም እንኳን ነፍሳቸው ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ወደ ሰማይ ትሄዳለች አለ።

6. ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣት የቻለው እንዴት ነው?
ሀ- ሕያው ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረው ኢየሱስ ስለሆነ ነው።

7. ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ለማስነሣት የወሰነው ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር በሞትም ላይ እንኳን ስልጣን እንዳለው ለሰዎች ሁሉ ለማሳየት ስለፈለገ ነው።

8. ኢየሱስን ለመግደል የፈለጉት እነማን ነበሩ?
ሀ- የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን።

9. የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ኢየሱስን እንዲገድሉት የመራቸው ማን ነበር?
ሀ- ሰይጣን።

- ሰዎች ሕጻናትን ወደ ኢየሱስ ማምጣት ወደዱ።

ማርቆስ 10፡13

13-ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው ሰዎች ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ ደቀመዛሙርቱ ግን ገሰጿቸው።

- ሕዝቡ ሕፃናትን ወደ ኢየሱስ ስላመጡ ደቀመዛሙርቱ የገሰጹአቸው ለምንድን ነው?

- ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ በሕፃናት መቸገር የለበትም ብለው ስለ አሰቡ።

- ኢየሱስ በሕፃናት ተቸግሯል?
-አልተቸገረም

-ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ምን አላቸው?

ማርቆስ 10፡14

14- ኢየሱስም ይህን ሲያይ ተቆጥቶ እንዲህ አላቸው፤ «ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ፤ አትከልክሏቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደእነዚህ ላሉት ናትና»።



- ኢየሱስ ሀብታሙ ወጣት ሀብቱን ከድሆች ይበልጥ እንደሚወድ ያውቃል።

- ኢየሱስ ሃብታሙ ወጣት ሀብቱን ከእግዚአብሔር ይልቅ እንደሚወድ ያውቃል።

- ሀብታችንን ከእግዚአብሔር ይልቅ ከወደድን እግዚአብሔር ያድነናል?
- አያድነንም

- ከዚያስ ሀብታሙ ወጣት ምን አደረገ?

ማርቆስ 10፡22-24

22-ሰውየው ይህን ሲሰማ ክፉኛ አዘነ፤ ብዙ ሀብት ስለ ነበረውም እየተከዘ ሄደ።
23-ኢየሱስ ዙሪያውን በመመልከት ደቀመዛሙርቱን «ለሀብታሞች ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት እንዴት ከባድ ነገር ነው!» አላቸው
24- ደቀመዛሙርቱም በንግግሩ ተገረሙ፤ ኢየሱስ ግን እንደገና መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «ልጆች ሆይ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት እንዴት ከባድ ነገር ነው!»

- ሀብታሙ ሰው እያዘነ የሄደው ለምን ነበር?

- ብዙ ሀብት ስለ ነበረው።

- እጅግ ብዙ የሆነውን ሀብቱን ለመስጠት ፈቃደኛ ስላልነበረ።

- ኢየሱስ ክፉ ልቡን እንዲለውጠው ፈቃደኛ ስላልነበረ።

- ምንም እንኳን ይህ ሀብታም ወጣት ልቡ በእግዚአብሔር ፊት መልካም እንዳልሆነ ባይረዳም ኢየሱስ ወደደው?

- ኢየሱስ ይህን ሀብታም ወጣት ለምን ወደደው?

- ኢየሱስ እርሱን ስለፈጠረ።

- ኢየሱስ ከክፉ ልቡ ሊያድነው ስለ ፈለገ።

- ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ስለሚወድ በውስጥ ካለው ከክፉ ልባቸው ሊያድናቸው ይፈልጋል።

- ከዚያስ ኢየሱስ ሀብታሙን ምን አለው?

ማርቆስ 10፡21ለ

21-[ኢየሱስ እንዲህ አለ]፤ «እንግዲያው አንድ ነገር ይጎዳሃል፤ ሂድና ያለህን ሁሉ ሽጥ፤ ለድሆችም ስጥ፤ በሰማይ የተከማቸ ሐብት ታገኛለህ፤ ከዚያ በኋላ ና ተከተልኝም» አለው።

- ኢየሱስ ሀብታሙ ወጣት ምን ማድረግ እንዳለበት ነገረው?

- ያለውን ሁሉ ሸጦ ለድሆች ሰጥቶ እርሱን እንዲከተለው ነገረው።

- ኢየሱስ እንዲህ ያለው ለምን ነበር ?

- ኢየሱስ ሀብታሙን ወጣት ከክፉ ልቡ ሊያድነው ስለፈለገ ነው።



- ኢየሱስ በደቀመዛሙርቱ ላይ የተቆጣው ለምን ነበር?

- ሕዝቡ ሕፃናትን ወደ እርሱ እንዳያመጡ ስለ ከለከሏቸው።

- ኢየሱስ ሁሉንም ሕፃናት ይወዳል?

- አዎን።

- ኢየሱስ ሁሉንም ሕፃናት የሚወደው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ሁሉንም ሕፃናት የፈጠረው ኢየሱስ ስለሆነ ነው።

- ሁሉንም ሕፃናት የፈጠረው ኢየሱስ ስለሆነ ሁሉንም ሕፃናት ሊያድን ይፈልጋል።

- ሕፃናትም የሰይጣን ባሪያዎች ሆነው በኃጢአት ተወልደዋል?

- አዎን።

- ሕፃናት ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ባርነት መዳን ያስፈልጋቸዋል?

- አዎን።

- ለዚህ ነው ሕፃናትም የእግዚአብሔርን ቃል መስማት የሚያስፈልጋቸው።

- ከዚያስ ኢየሱስ ስለ ሕፃናትና ስለ እግዚአብሔር መንግስት ምን ተናገረ?

ማርቆስ 10፡15-16

15- ኢየሱስ እንዲህ አለ «እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን
መንግስት እንደ ሕፃን የማይቀበል ሁሉ ከቶ አይገባባትም»።
16- ሕፃናቱንም አቀፋቸው፤ እጁንም ጭኖ ባረካቸው።

- ኢየሱስ «የእግዚአብሔርን መንግስት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም» ሲል ምን ማለቱ ነው?

- ኢየሱስ እኛ እንደ ሕፃን ልጅ በሆነ እምነት በእግዚአብሔር ካላመንን አንድንም ማለቱ ነው።

- የሕፃን ልጅ እምነት ምን ይመስላል?

- የሕፃን ልጅ እምነት ሙሉ በሙሉ የተሟላ እምነት ነው።

- የሕፃን ልጅ እምነት ከሙሉ ልብ የሆነ እምነት ነው።

- አንድ ሕፃን የእናቱን ጡት ሲጠባ እናቱን በሙሉ ልቡ ይታመንባታል።

- አንዲት ሕፃን በእናቷ ጀርባ ስትታዘል እናቷን በሙሉ ልቧ ትታመናለች።

- ኢየሱስ ሕፃን ልጅ በሙሉ ልቡ እናቱን እንደሚታመን ሁሉ እኛም በሙሉ ልብ በእግዚአብሔር መታመን እንዳለብን ገለጸ።

- በሙሉ ልባችን በእግዚአብሔር ካላመንን መዳን አንችልም።

- ኢየሱስ በመንገድ ላይ ሳለ አንድ ሀብታም ወጣት መጥቶ ኢየሱስን አንድ ጥያቄ ጠየቀው።

ማርቆስ 10፡17

17- ከዚያ ተነስቶ መንገዱን ሲጀምር፥ አንድ ሰው ወደ እርሱ እየሮጠ መጣ፤ በፊቱም በጉልበቱ ተንበርክኮ፥ «ቸር መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ ይገባኛል» አለው።

- ሀብታሙ ወጣት ኢየሱስን ምን ብሎ ጠየቀው?



- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ትዕዛዛቱን ሁሉ ሊጠብቁ እንደማይችሉ ያውቃል።

- ታዲያ እግዚአብሔር ትዕዛዛቱን ለምን ሰጣቸው?

- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በሙሉ መጠበቅ እንደማይችሉ ሊያሳያቸው ስለ ፈለገ ነው።

- ልባቸው በኃጢአት የተሞላ መሆኑን ሊያሳያቸው ስለ ፈለገ ነው።

- ልባቸው የበሰበሰ መሆኑን ሊያሳያቸው ስለ ፈለገ ነው።

- መልካም ሰዎች አለመሆናቸውን ሊያሳያቸው ስለ ፈለገ ነው።

- ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ቸር (መልካም) እንዳይደለ ሊያሳያቸው ስለ ፈለገ ነው።

- እኛ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ሁሉ በውጭ ለመጠበቅ ብንሞክርም እንኳን ልባችን በውስጥ የበሰበሰ ነው።

- እኛ መልካም ስራዎች እንዲኖሩን እጅግ ብንጥርም ልባችን በእግዚአብሔር ፊት ፈፅሞ መልካም ሊሆን አይችልም።

- ከዚያስ ኢየሱስ ምን አደረገ?

ማርቆስ10፡21ሀ

21-ኢየሱስም ተመለከተውና ወደደው።

19- ኢየሱስ እንዲህ አለ «ትዕዛዛትን ታውቃለህ፤ አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት አትመስክር፤ አታታልል፤ አባትህንና እናትህን አክብር»።

20- ሰውዬውም፥ «መምህር ሆይ፤ እነዚህን ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄአለሁ» አለው።

- ሀብታሙ ወጣት ምን መለሰ?

- ሁሉንም የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ከልጅነቱ ጀምሮ መጠበቁን ተናገረ።

- ይህ እውነት ነው?
- አይደለም

- ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በሙሉ መጠበቅ ይችላል።
- አይችልም።

- ሀብታሙ ወጣት ያልተረዳው ነገር ምን ነበር?

- ሀብታሙ ወጣት ያልተረዳው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በውጭ ቢጠብቅም ልቡ ግን ሁሉንም የእግዚአብሔር ትዕዛዛት በውስጡ እያፈረሰ መሆኑን ነው።

- ኢየሱስ «አንድ ሰው ሌላውን ሰው ከጠላ ያ ሰው ነፍሰ ገዳይ ነው» ብሎ አስተማረ።

- ኢየሱስ «ሰው ሴትን አይቶ ቢመኛት ያኔውኑ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል» ብሎ አስተማረ።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በምድረ በዳ ትዕዛዛቱን ለምን እንደ ሰጣቸው ታስታውሳላችሁ?



- «የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ምን ላድርግ?»

- ሀብታሙ ወጣቱ ኢየሱስን የጠየቀው ጥያቄ ምን ነበር?

- ኢየሱስን የጠየቀው የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ምን መልካም ሥራ መስራት እንዳለበት ነው።

- ኢየሱስን የጠየቀው የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት መክፈል ያለበት መልካም ስራ ምን እንደሆነ ነው።

- መልካም ስራችን ለዘላለም ሕይወት ያበቃናል?
- አያበቃንም

- መልካም ስራችን ለዘላለም ሕይወት ክፍያ ሊሆን ይችላል?
- አይችልም

- የኢየሱስ መልስ ምን ነበር?

ማርቆስ 10፡18

18- ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ «ለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ቸር የለም»።

- ኢየሱስ ሀብታሙ ሰው ለምን ቸር እንዳለው ጠየቀው።

- ቀጥሎም ኢየሱስ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር የለም አለው።

- ኢየሱስ እርሱ ቸር መሆኑን መካዱ ነበር?
- አይደለም።

- ኢየሱስ እርሱ አምላክ መሆኑን መካዱ ነበር?

- አይደለም

- ታዲያ ኢየሱስ እንዲህ ያለው ለምን ነበር?

- ኢየሱስ እንዲህ ያለው ሰዎች ሁሉ በኃጢአት ስለተወለዱ ቸሮች ሊሆኑ እንደማይችሉ ሀብታሙ ሰው እንዲረዳ ስለፈልገ ነው።

- በተጨማሪም ኢየሱስ እንዲህ ያለው ከኃጢአት ነፃ የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ መልካም እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ሀብታሙ ሰው እንዲረዳ ስለ ፈለገ ነው።

- ሀብታሙ ሰው የዘላለም ህይወት ማግኘት የሚችለው እንዴት ነው ብሎ አሰበ።

- መልካም ሥራ በመስራት።

- ሀብታሙ ወጣት ያልተረዳው ነገር ምን ነበር?

- ሀብታሙ ወጣት ያልተረዳው መልካም ስራዎች መልካም ሊያደርጉን አለመቻላቸውን ነበር።

- ሀብታሙ ወጣት ያልተረዳው መልካም ስራዎች የእኛን ክፋት ወደ መልካምነት ሊለውጡ አለመቻላቸውን ነበር።

- ሀብታሙ ወጣት ያልተረዳው በውጭ የምንሰራቸው መልካም ስራዎች በውስጥ ያለውን ክፉ ልባችንን ሊለውጡት አለመቻላቸውን ነበር።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡-

- አንድ ፍራፍሬ ውስጡ ከበሰበሰ ውጪውን ብናጥበው ውስጡ ለወጣል?
- አይለወጥም።



- ፍራፍሬው ውስጡ አሁንም እንደበሰበሰ ነው።

- አንድ ፍሬ በውስጡ ትሎች እየተርመሰመሱ በውጭ ያለውን ቆሻሻ ብንፈገፍገው ውስጡ ይለወጣል?

- አይለወጥም።

- ፍራፍሬው ውስጡ አሁንም በትል እንደተሞላ ነው።

- ሀብታሙ ወጣት በትላትሎች እንደተሞላና እንደበሰበሰ ፍራፍሬ መሆኑንና በኃጢያት መወለዱን አላወቀም።

- ሀብታሙ ወጣት በውጭ መልካም ስራዎችን ለመስራት ቢሞክርም ስራው በውስጥ ያለውን ክፉ ልቡን ሊለውጥ አይችልም።

- ኢየሱስ ሀብታሙን ወጣት ያስተማረው ሁሉም ሰው ከበሰበሰ ልብ ጋር ስለ ተወለደ ማንም ቸር ሰው ያለመኖሩን ነው።

- ልባችን በኃጢአት ከመወለዱ የተነሣ ምንም ዓይነት መልካም ሥራ ልባችንን አይለውጠውም።

- መልካም ስራዎችን በመስራታችን ጥሩ ሰዎች ልንሆን አንችልም።

- መልካም ስራዎች መልካም እንድንሆን አያደርጉም።

- ቀጥሎስ ኢየሱስ ምን አለ?

ማርቆስ 10፡19-20